# የባለአክሲዮኖች 21ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ

## ለተከበራችሁ የአጋር ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ ባለአክሲዮኖች

የአጋር ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ. ባለአክሲዮኖች 21ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በንግድ ህግ አንቀፅ 366፣367፣370 እና 372 መሠረት ጥቅምት 24 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ጀምሮ በራስ ሆቴል የመሰብሰቢያ አዳራሽ ስለሚካሄድ ባለአክሲዮኖች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በስብሰባው ላይ እንዲገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

**የአክሲዮን ማህበሩ ዓይነት** **የማይክሮ ፋይናንስ ስራ ላይ የተሰማራ የአክሲዮን ማህበር**

- የማህበሩ የተፈረመ ካፒታል 385, 274, 000
- የማህበሩ የተከፈለ ካፒታል 385, 274, 000
- የማህበሩ የምዝገባ ቁጥር LD/AA/3/0003015/2008
- የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት አድራሻ አ/አ ከተማ፣ ልደታ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ፡ 08፣ ዳማ ህንጻ 3ኛ እና 5ኛ ፎቅ

**የ21ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች**

1. ድምፅ ቆጣሪዎችን መሰየም
2. ምዕላተ ጉባዔው መሟላቱን ማረጋገጥ
3. የጉባዔውን አጀንዳዎች ማፅደቅ
4. በለቀቀ የቦርድ አባል ተተክቶ ስራ ላይ ያለ የቦርድ አባልን ሹመት ማጽደቅ
5. አዳዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበልና የነባር አክሲዮኖችን ግዥና ዝውውሮችን መወሰን
6. የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማጽደቅ
7. የውጭ ኦዲተሮችን ሪፖርት ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማፅደቅ
8. የውጭ ኦዲተሮችን መሾም እና ክፍያቸውን መወሰን
9. እ.ኤ.አ በ2023/24 ሂሳብ ዓመት የተጣራ ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ በዳይሬክተሮች ቦርድ በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን
10. እ.ኤ.አ የ2023/24 ሂሳብ ዓመት ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስለሚከፈል የተጣራ ትርፍ ድርሻ መወሰን
11. የ2024/25 በጀት ዓመት ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስለሚከፈል ዓመታዊ የሥራ ዋጋ መወሰን

12. የጉባዔውን ቃለ ጉባኤ ማፅደቅ

**ማሳሰቢያ፤**

- በጉባኤው ላይ በአካል መገኘት የማይችል ባለአክሲዮን ጉባኤው ከመካሄዱ ከሶስት ቀናት በፊት ልደታ ባልቻ ሆስታል ጀርባ ዳማ ሀውስ ህንጻ ላይ ሶስተኛ ፎቅ በሚገኘው የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት የፋይናንስና ኢንቨስትመንት መምሪያ ቢሮ ቁጥር 306 ቀርበው ለዚሁ ጉዳይ የተዘጋጀውን የውክልና ስልጣን መስጫ መሙላት ይችላሉ።
- እንዲሁም በውል እና ማስረጃ የተረጋገጠ በጉባዔ ላይ ለመካፈል እና ድምፅ ለመስጠት ግልፅ ስልጣን የሚሰጥ የውክልና ማስረጃ የያዘ ተወካይ በዕለቱ የውክልናውን ዋና እና ኮፒ እንዲሁም የባለአክሲዮኑን መታወቂያ ፎቶ ኮፒ ይዞ በመቅረብ በጉባዔው ላይ ለመሳተፍ ይችላል።
- በማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት ቀርባችሁ ውክልና የምትሰጡም ሆነ በጉባዔው በአካል የምትገኙ ባለአክሲዮኖች ማንነታችሁን የሚገልፅ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ፣ መንጃ ፈቃድ ወይም ፓስፖርት ይዛችሁ እንድትቀርቡ እንዲሁም በውክልና በጉባዔው ላይ የሚገኙ ተወካዮች ማንነታቸውን የሚገልፅ መታወቂያ ዋና እና ፎቶ ኮፒ ይዘው መገኘት ይኖርባቸዋል።

## የዳይሬክተሮች ቦርድ

## አጋር ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ